

# የስነምግባር ደምብ

## ታማኝነትን የተላበሰ መልካም ሥነምግባር

BUILDING TRUST

# ማውጫ


**የንግድ ስነምግባር ደንቦች** **6**

1. ሕጉን ማክበር 6
2. ጉቦና ሙስና ክልክል ነው 6
3. ስጦታዎች፣ መዝናኛዎችና ልገሳዎች 7
4. ፍትሃዊ ውድድር 8
5. የጥቅም ግጭትን ማስወገድ 9
6. የውስጥ አዋቂ ግብይት ክልክል ነው 9
7. ሚስጥራዊነትን፣ ደህንነትን እና የመረጃ ጥበቃ 10
8. የሲካ ንብረቶችን መጠበቅ 11
9. የሰብአዊ መብቶች እና የሰራተኛ ደረጃዎች፥ ፍትሃዊ ስራ ሁኔታዎች፣ ትንኮሳ እና አድልኦ 11
10. ጤናን፣ ደህንነትንና አካባቢን መጠበቅ 12
11. የንግድ አጋሮች 13
12. ማስመጣትና መላክ 13
13. ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር 13

**የትግበሪያ መመሪያ** **14**

14. ይህ ደንብ መከበሩን ማረጋገጥ 14
15. ሙሉ ለሙሉ ግልጽ መሆንና መናገር 14
16. አርኣያ መሆን 15
17. እነዚህን ደንቦች አለመተላለፍ 16
18. ጥርጣሬ ካደረብዎት ይጠይቁ 16
19. በማስተዋል መስራት፥ የጋዜጣ ሕግ 16
20. የአራቱን አይኖች መርህን መተግበር 16
21. ጥያቄዎች / አስተያየቶች 17




# የስነምግባር ደምብ

ውድ ጓዶች፣

ሲካ የቆመው **መተማመንን በመገንባት** ላይ ነው፡፡ ስነምግባር የተላበሰ ባህሪና ታማኝነትን የተላበሰ ንጹህ አቋም ለመተማመን መሰረት ይጥላሉ፡፡

ባልደረቦቻችን፣ ደንበኞቻችን፣ አቅራቢዎቻችን እና ባለአክሲዮኖቻችን ሁሉም በታማኝና ንጹህ አቋማችን ላይ ይመካሉ። የእርስዎ የስነምግባር ባህሪ ለሲካ ጥሩ ስም እና ለኩባንያውን የረጅም ጊዜ ስኬት የማዕዘን ድንጋይ ናቸው።

የስነምግባር ደንቡ በሲካ አለም አቀፋዊ አሰራር ላይ ታማኝነትን እና ስነምግባርን ለማበረታታት ያለመ ነው። የልዩ ባህላችን መሰረት የሆነውን የሲካ **እሴቶችን እና መርሆዎችን** ይገልፃል። ሲካ ከስነምግባር ውጭ ለሆነ ባህሪ ምንም አይነት ታጋሽነት የሌለው ሲሆን የሕግንም ሆነ የዚህ ደንብ ጥሰትን አይቀበልም፡፡

በዚህ በተሻሻለው የስነምግባር ደንብ ለዘላቂ እድገት፣ ለሰብአዊ መብቶችና ለአካባቢ ጥበቃ ያለንን ጠንካራ ቁርጠኝነት አጉልተን አሳይተንበታል፡፡

የእርስዎ ሚና፣ የሥራ ተዋረድ ደረጃ ወይም የሥራ ቦታ ምንም ይሁን ምን፤ የሥነ ምግባር ደንቡን አክብሮ መስራት እርስዎ ላይ የተጣለ የግል ሃላፊነት ነው ። ለሲካ ምንም ያድርጉ ምን፣ ምንጊዜም ቢሆን የዚህን ደንብ ቃልና መንፈስ ይከተሉ። አርአያ ይሁኑ እንዲሁም ሌሎች እንዲያደርጉ ተነሳሽነትን ይፍጠሩ!

ለተሳትፎዎ እና ለሲካ ስኬት ላደረጉት ጠቃሚ አስተዋፅዖ እናመሰግናለን።



Thomas Hasler
ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የሲካ ቡድን



Dr. Paul Hälg
የቦርዱ ፕሬዝዳንት፣ የሲካ ቡድን

ባራ፣ ሚያዚያ 2022

# ታማኝነትን የተላበሰ መልካም ባህሪ

## ሕግን በማክበር እንሰራለን

## በታማኝነት ላይ የተመሰረተ መልካም ሥነምግባራችን ላይ አንደራደርም

## በሥራችን ላይ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ደረጃዎችን ተግባራዊ እናደርጋለን

## እነዚህን መርሆዎች መከበራቸውን እናረጋግጣለን







**ይህንን የስነምግባር ደንብ ማክበር በሲካ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ የተጣለባቸው ግላዊ ሃላፊነት ነው**







## የንግድ ስነምግባር ደንቦች

### 1. ሕጉን ማክበር

- በስራችን ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑትን ሁሉንም ሕግጋቶችና መመሪያዎች በሚገባ ይከተሉ፡፡
- ተፈጻሚ ከሚሆኑ ሕግጋቶች የበለጠ ጥብቅ ቢሆንም እንኳ ይህን የስነምግባር ደንብና ሌሎች የውስጥ መመሪያዎችን በሚገባ ይከተሉ፡፡

*ተፈጻሚ የሚሆኑ ሕግጋቶችና እና ደንቦችን ሙሉ በሙሉ ማክበር የሁሉም ተግባሮቻችን ማዕቀፍ ነው። በተጨማሪም፣ ይህ የስነምግባር ደምብ ተፈጻሚ ከሚሆኑ ህጎች የበለጠ ጥብቅ ሊሆኑ የሚችሉ  ደንቦች ይገልጻል። እንዲሁም  ሊከተሏቸው የሚገቡ  ውስጣዊ መመሪያዎች አሉ፡፡*

### 2. ጉቦና ሙስና ክልክል ነው

- አንድ ሰው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር በማሰብ (ለምሳሌ ስራን ለመያዝ ወይም ለማግኘት) ወይም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት (ለምሳሌ ሲካ የሌለውን ፈቃድ) ማን ኛውንም ውለታ (ጥሬ ገንዘብ፣ ጉዞ፣ ስጦታ፣ ወዘተ) አታቅርቡ፡፡
- በሚወስኑት ውሳኔ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድርብዎ ወይም ያልተገባ ጥቅም እንዲሰጡ የሚመራዎ (ለምሳሌ፣ ለንግድ አጋርዎ ያልተገባ ቅናሽ) ማንኛውንም አይነት ውለታ (ጥሬ ገንዘብ፣ ጉዞ፣ ስጦታ፣ ወዘተ) አይቀበሉ።

*ሲካ ማንኛውንም ዓይነት ሙስናን ለመዋጋት ቁርጠኛ ነው። ሲካ ሰራተኞቹን፣ ወኪሎቹን እና ሲካን ወክለው የሚንቀሳቀሱ ሶስተኛ ወገኖችን በማንኛውም አይነት ጉቦ እንዳይሳተፉ ይከለክላል። ጉቦና ሙስና ብዙ መልክ ሊኖረው ይችላል። ገንዘብ ሊሆን ይችላል, እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ውለታ (ጉዞዎች, ማንኛውም አይነት ስጦታዎች)። ሁል ጊዜም ታስቦ የሚደረገው ተቀባዩ ግለሰብ ውለታውን ከሚውለው ግለሰብ ወይም አካል ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በተቀባዩ ሰው ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ተብሎ ነው። እንደዚህ አይነት ውለታ ቢውሉም ወይም ቢቀበሉ ያው ነው።  ይህን የሚያደርጉለት (መንግስት፣ ኩባንያ ወይም ግለሰብ) ቢሆን ምንም ለውጥ የለውም። ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ዓላማ ከሌላቸው የተለመዱ አይነት ስጦታዎችና መዝናኛዎች በስተቀር (ከዚህ በታች ተራ ቁጥር 3ን ይመልከቱ) ማንኛውም ውለታ ወይም ጥቅም የቱንም ያህል ትልቅ ወይም ትንሽ ቢሆን ምንም ለውጥ የለውም። እንዲሁም ጉቦ ወይም ሙስና ስለሆነ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡*

### 3. ስጦታዎች፣ መዝናኛዎችና ልገሳዎች

- ሕጋዊነት ያላቸው ምክንያታዊ የሆኑ፣ እና በሀገር ውስጥ ባለው የሲካ ድርጅት የስጦታና መዝናኛ ፖሊሲ መሰረት ብቻ ስጦታዎችንና መዝናኛዎችን ይስጡ ወይም ይቀበሉ፡፡
- በአካባቢዎ ያለውን የሲካ ድርጅት የስጦታና መዝናኛ ፖሊሲን የሚያከብር እስከሆነ ድረስ ስፖንሰር ማድረግና ለበጎ አድራጎት ተብሎ የሚደረግ ድጋፍ ይፈቀዳል፡፡
- የሲካን ገንዘብ ተጠቅሞ ለፖለቲከኞች፣ ለፖለቲካ እጩዎች ወይም ለፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ ማድረግ ክልክል ነው፡፡ የሲካ ስልት ወይም የስራ እንቅስቃሴ ላይ ድጋፍ ለሚኖራቸው የፖለቲካ ዘመቻዎች የሚደረጉ ልገሳዎች በቡድኑ አስተዳደር መጽደቅ አለባቸው፡፡

*በሁሉም አገሮች እና ገበያዎች ምክንያታዊ ስጦታዎች እና መዝናኛዎች (ምግብ፣ ስፖርት ወይም የባህል ዝግጅቶች ወዘተ) የተለመዱ የስራው አካል ናቸው፡፡ በተቀባዩ ግለሰብ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር የታቀደ ከሆነ ግን ጉቦ ይሆናል። የጉዞ ወይም የብዙ ቀን ዝግጅቶች እንዲሁም ለመንግስት ባለስልጣናት  የሚደረጉ ስጦታዎች እና የመዝናኛ ግብዣዎች ከአስጊ ሁኔታ ይመደባሉ። ሁሉም ኩባንያዎች ከዚህ ደንብ ማእቀፍ ስር ሆኖ፣ የተፈቀዱ የማፅደቅ ደረጃዎችን የሚገልጽ እና ከኮርፖሬት አብነት ፖሊሲ ጋር የሚስማማ የስጦታ እና መዝናኛ ፖሊሲ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡*



## 4. ፍትሃዊ ውድድር

- በገበያው ውስጥ አፈጻጸምን እና ፍትሃዊነትን መሰረት ያደረገ አሰራርን ደንበኞችም ጋር ሆነ እና ከአቅራቢዎች ጋር ተግባራዊ ያደርጉ፡፡
- በማንኛውም መልኩ ከተፎካካሪዎች ጋር በስትራቴጂዎች፣ ዋጋዎች፣ ገበያዎች፣ ደንበኞች፣ ምርቶች፣ የአመራረት ስልቶች ወይም ሌሎች ገበያ - ተኮር ገጽታዎች ላይ አይወያዩ፣ አይስማሙ ወይም አይተባበሩ፡፡
- ከሲካ ደንበኛ መልሶ የመሸጫ ዋጋ የአተማመን ሂደት ጋር በተያያዘ ጣልቃ ገብነት የተከለከለ ነው፡፡
- ማንኛውንም ስስ ጎን ያለው ግዴታን (ለምሳሌ ብቸኛ አከፋፋይነት፣ ያለ ተወዳዳሪ፣ የጋራ ሽርክናን) በተመለከተ ከኮርፖሬት ሕግ ክፍል ወይም ከድርጅቱ የህግ አማካሪ ጋር አስቀድመው ያረጋግጡ፡፡
- የገበያ - የበላይነትን አለአግባብ አይጠቀሙ፡፡

*ተፈጻሚ ለሚሆኑ የካርቴል እና የፀረ-እምነት ህጎች ሙሉ በሙሉ ተገዢ እንዲሆኑ እንጠብቃለን። ይህ በተለይ ከተወዳዳሪዎች ጋር በዋጋ ወይም በሌሎች ገበያ ተኮር ጉዳዮች ላይ ማንኛውንም ዓይነት ውይይት ወይም ስምምነትን ይመለከታል። መደበኛ ባልሆኑ ስብሰባዎች፣ ኮንፈረንሶች፣ የንግድ ትርዒቶች እና የንግድ ማህበራት ስብሰባዎች ወይም ሊኖሩ የሚችሉ የግዢ እድሎችን በሚያካትቱ ውይይቶች ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከተወዳዳሪዎች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች በህጋዊ መንገድ የተፈቀደ እስከሆነ ድረስ በዋና ስራ አስኪያጁ ተቆጣጣሪነት መተግበር እና በአግባቡ መመዝገብ አለባቸው።*



## 5. የጥቅም ግጭትን ማስወገድ

- በግል ወይም በቤተሰብ ፍላጎቶች እና በሲካ ፍላጎቶች መካከል የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ማንኛውንም ሁኔታ ያስወግዱ። እንደዚህ ያሉ ግጭቶችን ለአለቃዎ ሙሉ በሙሉ ይግለጹ፡፡
- ከሲካ ጋር ሊወዳደሩ የሚችሉ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ያስወግዱ፡፡
- የሲካ የስራ እድልን ለግል ጥቅም አያውሉ፡፡

*የግል ወይም በቤተሰብ ጥቅም፣ ሲካን በመወከል የሚደረጉ ውሳኔዎች ላየ ተጽእኖ ማሳደር የለበትም፡፡ ከሲካ ጋር ውድድር ሊፈጥር የሚችል ማንኛውም እንቅስቃሴ አይፈቀድም፡፡*

## 6. የውስጥ አዋቂ ግብይት ክልክል ነው

- የሲካ አክሲዮኖች፣ አማራጮች ወይም ቦንዶች ለመገበያየት ሚስጥራዊ፣ ዋጋ - ተኮር መረጃን አይጠቀሙ፡፡
- እንደዚህ ያለን መረጃ ለሶስተኛ ወገኖችም አያጋሩ፡፡
- የሲካ የንግድ አጋሮች አክሲዮኖችን፤ አማራጮችን ወይም ቦንዶችን ለመገበያየት ሚስጥራዊ፣ ዋጋ - ተኮር መረጃን አይጠቀሙ ወይም እንደዚህ ያለውን መረጃ ለሶስተኛ ወገኖች አያካፍሉ፡፡

*በውስጥ አዋቂ መረጃ ላይ የተመሰረተ ግብይት ልዩ መረጃን በመጠቀም ተገቢ ያልሆነ ትርፍን ያስገኛል። ይህ በስዊዘርላንድ እና በሌሎች በርካታ ሀገራት ህገወጥ ነው። የውስጥ ንግድ ግብይት በዋናነት በሲካ አክሲዮኖች መገበያየትን ይመለከታል። ነገር ግን የሲካ የንግድ አጋሮችን አክሲዮኖች ለመገበያየት የውስጥ አዋቂ መረጃ መጠቀምንም ይከለክላል። **የሲካ የውስጥ ንግድ እና አስተዳደር የግብይት ፖሊሲ** (Sika Insider Trading and Management Transactions Policy) በተለይ ከንግድ ውጪ ያሉ ወቅቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መመሪያ አስቀምጧል፡፡*

## 7. ሚስጥራዊነትን፣ ደህንነትን እና የመረጃ ጥበቃ

- የሲካ ሚስጥራዊ የንግድ፣ የቴክኒክ እና የፋይናንስ መረጃዎችን ይጠብቁ፡፡
- በሲካ ውስጥ ሚስጥራዊ መረጃን ማወቅ በሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ ብቻ ያጋሩ፡፡
- አላማው ለስራ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘና ሚስጥር የመጠበቅ ስምምነት ካልተፈረመ በስተቀር ሚስጥራዊ መረጃን ለማንኛውም ሶስተኛ ወገን አያጋሩ፡፡
- **በሲካ ግሩፕ የአይቲ ፖሊሲ** *(Sika Group IT security policies and directives)* መሰረት የሚስጥራዊ መረጃ ደህንነት በትክክለኛውና በቂ በሆነ መንገድ መጠበቁን ያረጋግጡ።
- የሶስተኛ ወገኖች እንዲሁም የሰራተኞቻችን ሚስጥራዊ መረጃና የግል ዳታ ይጠብቁ፡፡
- በሲካ የተሰበሰበው የግል መረጃ ፍትሃዊ በሆነ መንገድና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መያዙን ያረጋግጡ፡፡
- በአካባቢው የሚተገበሩ የመረጃ ጥበቃ ህጎችን ያክብሩ እና የሲካ የውስጥ የመረጃ ጥበቃ መመሪያዎችን ያክብሩ፡፡

*የሲካ እውቀትን መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ሲካ ለንግድ ስራው የሚያስፈልገውን የመረጃ ፍሰት ለማደናቀፍ ባይፈልግም ፣ የሲካ እውቀትን አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል መከላከል በጣም አስፈላጊ ነው። እኩል በሆነ መንገድ የሶስተኛ ወገኖችን ሚስጥራዊ መረጃ እንጠብቃለን።*




## 8. የሲካ ንብረቶችን መጠበቅ

- የሲካ ንብረቶችን (መገልገያ መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ መኪናዎች፣ ወዘተ) በጥንቃቄ ይያዙ እንዲሁም በበላይ አለቃዎ ካልተፈቀደ በስተቀር ለስራ ጉዳይ ብቻ ይጠቀሙ፡፡
- የሲካ ንብረቶችን አላግባብ ጥቅም ላይ ከማዋል (ማጭበርበር፣ ስርቆት፣ ኪሳራ) ይጠብቁ፡፡

## 9. የሰብአዊ መብቶች እና የሰራተኛ ደረጃዎች፤ ፍትሃዊ ስራ ሁኔታዎች፣ ትንኮሳ እና አድልኦ

- የአለም አቀፍ የስራ ደረጃዎችን የሚያንፀባርቁ የሰራተኛ ቅጥር ሕግጋቶችን እንዲሁም የሲካ የውስጥ ፖሊሲዎችን በሙሉ ያክብሩ፡፡
- የበታቾችዎን እና የስራ ባልደረቦችዎን በፍትሃዊነት እና በአክብሮት ይያዙ፡፡
- ፈጠራን፣ ግልጽነትን እና የእኩልነት እድሎችን ለማመቻቸት የሚያስችል በብዝሃነት እና በመተማመን ላይ የተመሰረተ አካታች ባህልን በማስተዋወቅ ላይ ይሳተፉ፡፡
- ሌሎችን በዘራቸው፣ በዜግነታቸው፣ በጾታዊ ፍላጎታቸው፣ በጾታቸው፣ በእድሜያቸው፣ በሃይማኖታቸው ወዘተ . ላይ ተመስርተው ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ አያስተናግዱ እንዲሁም ወይም በቃላት ወይም በአካል አይጉዱ፣ ጥቃት አያድርሱ፣ አያሳዝኑ፣ አያስፈራሩ ወይም ስጋት ላይ አይጣሉ፡፡
- ማንኛውንም አይነት ጥቃት ወይም በሰራተኞች ላይ የሚደረግ አድልዎን አይፍቀዱ እንዲሁም ጥሰቶች ከታዩ ለአለቃዎ ወይም ለሰው ሃይል አስተዳደር ሪፖርት ያድርጉ፡፡

*ሲካ ሁሉም ሰራተኞች እርስበርሳቸው ፍትሃዊ በሆነ መንገድና በአክብሮት የሚስተናገዱበት ብዝሀነት የተላበሰና ሁሉንም አካታች የሆነ የስራ አካባቢ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ሲካ እድልን በእኩልነት ለመስጠት ቁርጠኛ ሲሆን ጾታዊ እንዲሁም ሌሎች በስራ ላይ የሚፈጸሙ ትንኮሳዎችን በጥብቅ ይከለክላል፡፡ ሲካ የሁሉም ሰራተኞች ምግባር በአለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት ከተደረሰባቸው የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶች እንዲሁም ከዋና ሰራተኛና ማህበራዊ ደረጃዎች* ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ የሚፈልግና የተባበሩት መንግስታት በአለም አቀፍ ውስን አስር መርሆዎችን ይደግፋል፡፡*
*ሲካ ሁሉንም አይነት የሕጻናትንና የግዳጅ ስራን ማስወገድ ላይ (ዘመናዊ ባርነትንና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ጨምሮ) - እንዲሁም በራሱ የአቅርቦት ሰንሰለት መረብ ውስጥና ፤የመደራጀት ነጻነት፣ የጋራ ድርድርና ማህበራዊ አጋርነት፣ ፍትሃዊ ካሳና ፍትሃዊ የስራ ሰአት እንዲኖር ቁርጠኛ አቋም አለው፡፡*

** እነዚህ መመዘኛዎች ሁለንተናዊ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ የ OECD መመሪያዎች የብዙሀን አቀፍ ኢንተርፕራይዞች እና የአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (አይኤልኦ) የብዝሃ-ሀገራዊ ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራዊ ፖሊሲን በሚመለከቱ መርሆዎች የሶስትዮሽ መግለጫን ያካትታሉ፡፡*

## 10. ጤናን፣ ደህንነትንና አካባቢን መጠበቅ

- የአካባቢ፣ የጤና እና የደህንነት ህጎችን እና ተዛማጅ የውስጥ መመሪያዎችን ያክብሩ።
- የደህንነት ባህልን ያስተዋውቁ እና በደህንነት እና ሌሎችን በመጠበቅ ላይ በጭራሽ አይደራደሩ ።
- የሀብት ዘላቂ አጠቃቀምን ማሳደግ እና ዘላቂነት ባለው የንግድ ልምዶች ውስጥ በመሳተፍ ፤ ሲካ በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ (አየር፣ ብክነት፣ ውሃ፣ ሃይል ፍጆታ እና ብዝሃ ህይወት) በመቀነስ፣ ለክብ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ በማድረግ እና ለአካባቢ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ቅድሚያ መስጠት ።
- ከደህንነት፣ ከጤና እና ከአካባቢ ጥበቃ ይልቅ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው በፍጹም አይፍቀዱ።

*የሰራተኞች ደህንነትና በመልካም ሁኔታ ላይ መሆን ለሲካ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ነው። ሲካ ስራውን የሚያካሂደው ዘላቂና ማህበራዊ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ነው። ሲካ ለሰራተኞቹ ፣ለደንበኞቹ እና ለህብረተሰቡ በአጠቃላይ እና ለፕላኔታችን የወደፊት ሁኔታ በማሰብ የጤና ፣የደህንነት እና የአካባቢ ህጎችን እና የውስጥ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ የማክበር ሀላፊነት አለበት።*



## 11. የንግድ አጋሮች

- አቅራቢዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ወኪሎችና አከፋፋዮች ለእነዚህ ደንቦች ተገዢ መሆናቸውን ያረጋግጡ።
- የደንበኞችን በተልይም የስጦታና መዝናኛ ደንቦች ከዚህ የስነምግባር ደንብ እና ከአካባቢያችሁ የስጦታና መዝናኛ ፖሊሲ በተለይም በስጦታና በመዝናኛ ረገድ የበለጠ ጥብቅ ቢሆኑም እንኳ ያክብርዋቸው።

*ሲካ የስራ ላይ አጋሮቹና አቅራቢዎቹ በታማኝነት ስራቸውን እንዲያካሂዱና ተመሳሳይ የስራ ላይ ስነምግባር ደንቦችን እንዲከተሉ ይጠብቃል። ይህንን ግብ ለመምታት፣ የሲካ አቅራቢዎች **የሲካ የአቅራቢዎች የስነምግባር ደንብን** (Sika Supplier Code of Conduct) ማክበር ይኖርባቸዋል። ሲካ ለአቅራቢዎቹ ስልጠና በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፤ በዚህም ላይ የሚኖራቸውን ተገዢነት በመጠይቅና ኦዲት ይቆጣጠራል።*

## 12. ማስመጣትና መላክ

- ተፈጻሚ የሚሆኑ ማዕቀቦች እንዲሁም ያለመስፋፋት፣ ከውጭ የሚመጡ እና ወደ ውጭ በሚላኩ ዕቃዎች ላይ የሚደርግ ቁጥጥር እና የአደገኛ እቃዎች ደንቦችን ያክብሩ።
- የጉምሩክ ትክክለኛ ሰነዶችን ያረጋግጡ እንዲሁም ሁሉንም አስፈላጊ የጉምሩክ ፈቃዶችን ይያዙ።

*ሲካ ተፈጻሚ የሆኑ ሁሉንም የንግድና የጉምሩክ ደንቦችን መከተሉን ለማረጋገጥ ይተጋል፣ የተለያዩ የሃገር ውስጥና የአለም አቀፍ የንግድ ሕግጋቶች ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለማስመጣትና ለመላክ ገደብ ይጥላሉ ወይም ክልከላ ያደርጋሉ። እንደዚህ ያሉ እገዳዎች በምርቱ ባህሪ ላይ ብቻ ሳይሆን የሚመጣበትን ሀገር ወይም መዳረሻ ላይ እንዲሁም አልፎ አልፎ በደንበኛውና በአቅራቢዎች ማንነት ላይ (ማእቀቦች) ጭምር ተመስርተው የሚደረጉ ናቸው።*

## 13. ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር

- ማንኛውንም አጠራጣሪ የገንዘብ ልውውጥን በንቃት ወዲያውኑ ለበላይዎ ውይም ለፋይናንስ ተቆጣጣሪ ሪፖርት ያድርጉ።

*ሲካ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመዋጋት ቁርጠኛ ነው። ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ማለት ከወንጀል ተግባራት የሚመነጩ ንብረቶችን (ጥሬ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን) ወደ መደበኛው የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ስርአት ማስገባት ማለት ነው። ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል ነው።*

## የትግበሪያ መመሪያ

### 14. ይህ ደንብ መከበሩን ማረጋገጥ

- ይህ የስነ ምግባር ደምብ ለሁሉም የሲካ ሰራተኞች የሚሰራ ሲሆን ሁሉም አዲስ ሰራተኛ ይህን የስነ ምግባር ደምብ መመሪያ ሊያውቅ፤ ጥቅሙን ሊረዳና ራሱን ለዚህ ሊያስገዛ ይገባል።
- በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰራተኞች እነዚህን ሕግጋቶች በተመለከተ ቢያንስ በአመት አንዴ በመደበኛነት እንዲያስታውሱ ይደረጋል።
- የሲካ ድርጅት ሁሉም ዋና ስራ አስኪያጆች የሚመሩት ድርጅት እነዚህን ሕግጋቶች እያከበረ መሆኑን ያረጋግጣሉ።
- የኮርፖሬት የስራ ክፍሎች መደበኛ የሆኑ ስልጠናዎችን እንዲሁም ኦዲቶችን ያካሂዳሉ።

*ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊ መሳሪያዎችን እና ዘዴዎችን የሚያቀርብ ሲሆን ፣ ይህንን የስነምግባር ደንብ ማክበር የየደረጃው ሀላፊ ቀጣይነት ያለው ኃላፊነት ነው። በዚህ ረገድ ትክክለኛ የሰው ሀይል መረጣ፣ ስልጠና እና ክትትል ወሳኝ ነው።*

### 15. ሙሉ ለሙሉ ግልጽ መሆንና መናገር

- ማንኛውንም አይነት የግብይት ልውውጥ በትክክል ያውጁ እና ይመዝግቡ።
- ከእነዚህ ደንቦች ጋር ሊጋጭ የሚችል ማንኛውንም ሁኔታ ለበላይዎ ያሳውቁ
- የእነዚህን ደንቦች መጣስ ለበላይዎ፣ ለሰው ሃብት ወይም ለድርጅቶ አስተዳደር አባል ሪፖርት ያድርጉ፣ ወይም - ውጤታማ ካልሆነ ወይም የሚቻል ካልሆነ፣ ወደ ቀጣዩ የአስተዳደር ደረጃ ይሂዱ። በኢሜል (compliance@ch.sika.com) ወይም በሲካ ትረስት መስመር በኩል (https://) sikatrustline.com) ወደ ኮርፖሬት ተገዢነት ተቆጣጣሪ ክፍል ማመልከት ይችላሉ።
- በቅንነት መረጃ የሚሰጡ ሰዎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው የመረጃው ምንጭ ሚስጥር ተደርጎ የሚያዝ ሲሆን፤ ከዚህ መመሪያ ውጭ የሚያፈነግጥ ሰራተኛ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል ።

*በሲካ፣ ክፍት እና ሙሉ ግልጽነት ያለው ድባብ ፈጥረናል። ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶች እና የተገኙ ጥሰቶች ላይ ግልጽ መሆን ይህንን የስነምግባር ህግ ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል። ሁሉንም ግብይቶች በትክክል መመዝገብ እና የሂሳብ አያያዝን በተመለከተም ግልፅነት አስፈላጊ ነው። **በሲካ ትረስት ፖሊሲ** (Sika Trust Policy) ውስጥ በተቀመጡት መርሆች መሰረት ሁሉም ሰራተኞች እንዲናገሩ እና ለበላይዎቻቸው፣ ለሰው ሃይል አስተዳደር ወይም ለሌላ ማንኛውም የድርጅቱ አስተዳደር ቡድን አባል ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን በተገቢውና በወቅቱ እንዲያሳውቁ እናበረታታለን ።የተጠረጠሩ ጥሰቶች በጥንቃቄ ይሚመረመሩና በተጨባጭ ከተረጋገጡ ተሳታፊ በነበሩ ግለሰቦች ላይ (ከስራ መሰናበትን ጨምሮ) ተከትለው የሚመጡ የስነምግባር እርምጃዎች የሚኖሩ ሲሆን ይህን መሰል ጥሰትን በቅን ልቦናና በምክንያታዊነት ሪፖርት የሚያደርጉ ግለሰቦችን ሊደርስባቸው ከሚችል በቀል ጥበቃ ያገኛሉ።*

### 16. እርኣያ መሆን

- የበላይ አካል እንደመሆንዎ መጠን አርአያ መሆንና የስነምግባር ደንቡንም በጥብቅ መከተል ይኖርብዎታል።
- በተሰጥዎት የኃላፊነት ቦታ ላይ ማንኛውንም ጥሰት የሚከለክል ፖሊሲን ተፈጻሚ ያድርጉ።
- ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ላይ በቅድሚያ ለመፍታት እንዲቻል በግልጽነት ላይ ይስሩ።

*በዚህ የስነምግባር ደንብ ላይ ሕይወትን ለመዝራት የበላይ አካል ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው፡ ፡ አርአያ መሆንና ማንኛውንም ጥሰት የማይፈቅድ ፖሊሲን መተግበር አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ሊከሰቱ የሚችሉ ጥሰቶችን በግልጽና ተገቢ በሆነ መንገድ ሊፈቱ የሚችሉበት የስራ አካባቢ እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ነው።*



## 17. እነዚህን ደንቦች አለመተላለፍ

- እነዚህን ደንቦች ለመጣስ ሶስተኛ ወገኖችን አይጠቀሙ።

*እነዚህን ደንቦች ለመጣስ ወሳኝ ምግባር ወይም የንግድ ሥራ ለሶስተኛ ወገኖች (ለምሳሌ ወኪሎች፣ አከፋፋዮች፣ አማካሪዎች) በውክልና ሊሰጥ አይገባም።*

## 18. ጥርጣሬ ካደረብዎት ይጠይቁ

- በማንኛውም ጊዜ ጥርጣሬ ካደረብዎት ይጠይቁ።

*በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች የሕጎችን ወይም የውስጥ ደንቦችን መጣስ በወቅቱ ምክርን በመጠየቅ ሊወገድ ይችላል። የትኛውን ውሳኔ መወሰን ወይም እርምጃ መውሰድ እንዳለቦት ጥርጣሬ ካደረብዎት መጀመሪያ ሌሎችን ይጠይቁ እንዲሁም አለቃዎን ወይም ከሚመለከተው መምሪያ (ለምሳሌ፡ የሰው ሀብት፣ ሕግ፣ ተገዢነት ተቆጣጣሪ ወይም ፋይናንስ) ምክር ወይም እገዛን ይጠይቁ።*

## 19. በማስተዋል መስራት፡ የጋዜጣ ሕግ

- የተለየ ህግ ከሌለ ወይም ጥርጣሬ ካደረብዎት እርምጃዎን በቀላሉ በጋዜጣ ሕግ ያረጋግጡ፡ ድርጊትዎ ከነሙሉ ዝርዝሩ በአከባቢዎ ጋዜጣ የፊት ገጽ ላይ ቢወጣ ያደርጉታል?

*አብዛኛዎቹ እነዚህ ደንቦች ውስን ሊሆኑ ቢችሉም እንዲሁም ሊከተት የሚችለውን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ባይሸፍኑም፣ የጋዜጣው ህግ በአለም አቀፍ ደረጃ መረዳት የሚቻልና ተግባራዊ የሚሆን ነው። አንድ ስነምግባር ይፈቀዳል ወይም አይፈቀድም በሚለው ላይ ትክክለኛ ምልከታ ይሰጣል።*

## 20. የአራቱን አይኖች መርህን መተግበር

- በሲካ ስም የሚካሄዱ ስራዎች - በወረቀትም ሆነ በዲጅታል መልኩ ቢሆን - ምንም እንኳን የአካባቢያዊው ሕግ የሚፈቅደው አንድ ፊርማ ብቻ ቢሆንም ስልጣኑ ባላቸው በሁለት ሰዎች መፈረም አለበት።
- ስራው የሚኬሄደው በኤሌክትሮኒክ ግንኙነት (ኢሜል፣ የጽሑፍ መልእክት፣ ወዘተ) ከሆነ መፈረም የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው። ነገር ግን፣ ሁለተኛ ሰው ስራው ከመላኩ በፊት ገምግሞ ማጽደቅ ይኖርበታል።
- በአካባቢው ህግ ካልተፈለገ በስተቀር ቸፐስ ወይም የግል ማህተሞችን በጭራሽ አይጠቀሙ፣ ቸፐስ/ማህተም የሚጠቀሙ ከሆነ ሁልጊዜ የግል ፊርማዎን አብረው ያካቱ።

*የአራት አይኖች መርህ የሲካ ትክክለኛው የስጋት አስተዳደርና የስነምግባር ቁልፍ መርህ ነው። ብቃት ያለቸው ሁለተኛ ጥንድ አይኖች የንግድ ጉዳዮችን መገምገም፣ አግባብነት ያለው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ማረጋገጥ እና በተለይም ከዚህ የስነምግባር ደንብ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ አለባቸው።*

## 21. ጥያቄዎች / አስተያየቶች

ይሄን የስነምግባር ደንብ በማስመልከት ጥራጣሬ ወይም ጥያቄዎች የሚኖርዎት ከሆነ የበላይዎን ወይም ኮርፖሬትን ያነጋግሩ። ጥያቄዎችዎንና አስተያየቶችዎን በ compliance@ch.sika.com. ላይ መላክ ይችላሉ።





# የስነምግባር ደምብ

## ታማኝነትን የተላበሰ መልካም ሥነምግባር

BUILDING TRUST

Sika®